# ቅንጅት በሁለት እግሩ ቆሞ ታሪካዊ ግዴታውን እንዲወጣ አስተዋጽኦ ማድረግ ከሁሉም ይጠበቃል፡፡

## ከአዲስ አበባ የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፐርቲ አባላት የተሰጠ መግለጫ

የአራት እውቅ የፖለቲካ ድርጅቶች ውህድ የሆነው ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፐርቲ የግንቦት 97 አገራዊና ክልላዊ ምርጫን በህዝብ ፍላጎት ለአሸናፊነት የበቃበትን ሂደት መለስ ብለን ስናስተውል ልባችን ዛሬም በኩራትና በአድናቆት ይሞላል፡፡ ምንም እንኳን የምርጫው ፍፃሜ ፐርቲያችንና የመረጠው ህዝብ እንደተመኙትና እንደጠበቁት ባይሆንም የኢትዮጵያ ህዝብ በነቂስ ወጥቶ በድምፁ ያስተላለፈው መልዕክት ለውጥ መፈለጉን ከልብ እንድንገነዘብ አስችሎናል፡፡ ቅንጅት ለዚህ ያበቃው የሚመራባቸው የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የዴሞክራሲ መርሆቹና የኢትዮጵያ ህዝብ ያልተቋረጠ ድጋፍ ናቸው፡፡

ህዝቡ ለቅንጅት ለሰጠው ድጋፍና ላሳየው አለኝታነት ከፍተኛ አክብሮትና ምስጋና እናቀርባለን፡፡ ሁሉም እንደሚያውቀው ፐርቲያችን ቅንጅት ከተመሰረተበት ጊዜ አንስቶ ከውስጥም ከውጭም በርካታ ችግሮች ገጥመውታል፡፡ ለዛሬ የደረሰውን ችግሮቹን እንደአመጣጣቸው በሰከነ አካሄድ እያስተናገደ ነው፡፡ ቅንጅት ህዝብ በውል የተገነዘበውን አላማውን ከዳር ለማድረስ ከሚመራባቸው መርሆዎች መካከል ህጋዊነት፣ ዴሞክራሲያዊ የጋራ አመራር፣ የአሠራር ግልጽነትና መልካም ሥነ-ምግባር ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ለእነዚህ መርሆዎች ተገዢ መሆን ያልቻሉ ግለሰቦች በሀገር ደረጃም ሆነ በፐርቲው ውስጥ መርሆዎቹ እንዳይተገበሩ የተቻላቸውን አድርገዋል፡፡ እያደረጉም ይገኛሉ፡፡

እኛ በአዲስ አበባ አስሩም ክ/ከተማዎች የምንገኝ የቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ፐርቲ አባላት የቅንጅት ላዕላይ ም/ቤት ታህሣሥ 23/2000 ዓ.ም ባወጣው መግለጫ-

1. የተጓደሉት የላዕላይ ም/ቤት አባላትን ስለማሟላት፣

2. የፐርቲውን ህጋዊነት ስለማረጋገጥ፣

3. ሊቀመንበሩ ስለወሰዷቸው ህገ-ወጥ እርምጃዎች

በሚሉ ወቅታዊና አንገብጋቢ ጉዳዮች ላይ በሰፊው መክሮ የጋራ ግንዛቤ መያዙንና ውሳኔዎችን ማሳለፉን በውል ተገንዝበናል፡፡ ከዚህም ውሣኔ ላይ የተደረሰው የቅንጅት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ለሦስት ጊዜ የላዕላይ ም/ቤት ስብሰባ ጠርቶ በሦስተኛው ጊዜ በተገኙ አባላት ገዢ ውሳኔ እንደሚያስተላልፍ ባሳወቀው መሠረት እንደሆነ ለማወቅ ችለናል፡፡ በመሆኑም...

1ኛ/ በተጓደሉ የላዕላይ ም/ቤት አባላት ምትክ ስለማሟላት

የላዕላይ ም/ቤቱ ከቅንጅት ለአንድነትና ለዴክራሲ ፐርቲ ጠቅላላ ጉባኤ የተቀበለውን አደራና ኃላፊነት መወጣት የሚጠበቅበት ሲሆን ይህን ኃላፊነት ሊወጣ የሚችለው በመተዳደሪያ ደምቡ መሠረት በቀጥር ተሟልቶና በሰው ኃይል ተጠናክሮ ሲገኝ ብቻ እንደሆነ እንረዳለን፡፡ በሰው ኃይሉ የተመናመነ ላዕላይ ም/ቤት የጋራ አመራር ለመስጠት እንደሚቸገር የታወቀ ነው፡፡ በተለይ ዛሬ

ፐርቲው በችግር ውስጥ በሚገኝበትና የፐርቲው ህጋዊነት ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የፐርቲውን የህጋዊነት ጉዳይ በአስቸኳይ ለመወሰን የሳዕሳይ ም/ቤቱን የማሟሳት ሥራ ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር ነው፡፡ ስለሆነም ፐርቲው የገጠመውን ውስጣዊና ውጫዊ ችግሮች አስወግዶ አሳማውን ከግብ ለማድረስ ሳዕሳይ ም/ቤቱ በአስቸኳይ ቁጥሩ ተሟልቶና ተጠናክሮ ሥራ እንዲጀምር ሳዕሳይ ም/ቤቱ ያስተሳለፈውን ውሳኔ ከልብ እንደግፋለን፡፡

2ኛ/ የርቲውን ህጋዊነት ስለማረጋገጥ

የፐርቲውን ህጋዊነት የማረጋገጥ ጉዳይ የወቅቱ ዐብይ ተግባር ነው፡፡ ይህ ሥራ ደግሞ ለነገ የሚባል ሳይሆን በተቻለ ፍጥነት ሊከናወን የሚገባው ነው፡፡ በግንቦት 97 ዓ.ም ምርጫ አብሮን ደፋ ቀና ሲል የነበረው ህዝብ ዛሬም እንደትናንቱ የቅንጅትን አመራር ይሻል፡፡ «እጃችሁን ከምን» እያለንም ነው፡፡ ስለሆነም ቀደም ሲል የፐርቲውን ህጋዊነት በአጭር ጊዜ ለማረጋገጥ የሚያስችሉ አቅጣጫዎችን በማጥናት የደረሰበትን ውጤት የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ለሳዕሳይ ም/ቤቱ እንዲያቀርብ መወሰኑን ከልብ ተቀብለነዋል፡፡ በዚህም ረገድ የሚሠራው ሥራ ፈጣን እንዲሆን ሳዕሳይ ም/ቤቱንና ሥራ አስፈፃሚውን ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡

3ኛ/ ሊቀመንበሩ ኢ/ር ኃይሉ ሻውል የወሰዷቸውን እርምጃዎች በተመለከተ

የአንድ ፐርቲ ህልውና ጤናማነት የሚረጋገጠው ፐርቲው እራሱ ሳወጣው ደንብ እና ፕሮግራም ተገዢ መሆን ሲችል ነው፡፡ ይህ በሌለበት ስለ አንድ ድርጅት ውስጠ ርቲ ዴሞክራሲ ማውራት በእጅጉ ይከብዳል፡፡ ፐርቲያችን ቅንጅት በአባላት ምርጫ የሥራ ኃላፊነትና ሥልጣን የያዙ የፐርቲ አመራር አባላት ያሉት ሲሆን በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ የኃላፊነት ደረጃቸውና የሥልጣን ገደባቸው በውል ተቀምጧል፡፡ ይህ ከሆነ ዘንዳ ደንቡ በውል ሊተገበር ይገባል እንላለን፡፡ የመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 9.3.18 በፐርቲው ሊቀመንበር፣ ተቀዳሚ ሊቀመንበር፣ ም/ሊቀመንበር ዋና ፀኃፊና ሌሎች የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ሳይ እርምጃ መውሰድ የሚችለው ሳዕሳይ ም/ቤት መሆኑን፤ ይህም ሲሆን የሚችለው በ2/3ኛ ድምፅ መሆኑ እየታወቀ የፐርቲው ሊቀመንበር ኢንጂነር ኃይሉ ሻውል በአምስት የሳዕሳይ ም/ቤትና የሥራ አስፈፃሚ አባላት ሳይ የእገዳ እርምጃ መውሰዳቸው፤ ከዚህም ባሻገር በቦታቸው ተተኪ መሠየማቸው የፐርቲውን ደንብ ያልተከተለ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ እንደዚህ ያለው የአንድ ግለሰብ ብቸኛ አሠራር የጋራ አመራርን የሚፃረርና ደብዛውን የሚያጠፋ በመሆኑ በአስቸኳይ ሊታረም ይገባል እንላለን፡፡ ከዚህም ስህተት ሌሎችም ትምህርት እንዲወስዱ ማሳሰብ እንወዳለን፡፡

በጠቅላላ ጉባኤ መሀል ባለው ጊዜ ፐርቲውን የመምራት ሁነኛ ኃላፊነት የቅንጅት ሳዕሳይ ም/ቤት ነው፡፡ ሳዕሳይ ም/ቤቱ የሚሰጠውን ውሳኔ ከ እስከ ሳይባል ማንኛውንም የቅንጅት አመራርን ሆነ አባል የሚገዛ ውሳኔ ነው፡፡ ለፐርቲው ሥራ መቃናትና ውጤታማነት በተለይ ከቅንጅት አባላት ብዙ ይጠበቃል፡፡ በህዝቡ ውስጥ የሰረፀን ድርጅት አፈርሳለሁ ብሎ መዶለት የማይሳካ ነገር ግን ለአጉል ትዝብት የሚዳርግ እኩይ ተግባር በመሆኑ ይህን የሚያስቡ ሁሉ እንዲጠነቀቁ እንመከራለን፡፡ ይልቁኑም የቆምንለትና መስዋዕትነትን የከፈልንበትን ድርጅት ክቡር አላማ ከዳር ለማድረስ በጽናት ተሰልፈን ታሪካዊና አገራዊ ግዴታችንን እንድንወጣ እንዲሁም ለቅንጅት አላማ ስኬት በቁርጠኝነት የቆመውን ህዝብ ወቅቱ በሚጠይቀው የትግል ደረጃ መጠን እናታግለው እያል ጥሪያችንን እናስተሳልፋን፡፡

ለቅንጅት አንድነትና አይበገሬነት ሁላችንም በአንድነት እንነሣ!!